# የህፃኑ ጥሪ

andualem19@yahoo.com

በረንዳ ቢወጣ--እጉዋዳ ቢገባ፣

ቢጣራ ቢጣራ--አስሬ ቢል ባባ፣

እናቱን ቢያስጨንቅ--ፊቱ ተጥቦ በ'ንባ፣

ዉስጧ ቢተራመስ--የሷም ሆድ ቢባባ፣

መልስ ግን የላትም--ታዉቀዋለችና፣

ለጊዜዉ አይመጣም………………

እዉነትን ፍለጋ--ትግል ላይ ነዉ ባባ::

ዉጣ ችላዉ እንጂ--እሷስ ምን ታድርገዉ፣

ቀን ዘሞባት እንጂ--እሷስ መቼ ፈቅዳዉ፣

ምን ብላ ትዋሸዉ--እነደምን ታባብለዉ፣

ያን ቆሻሻ ታሪክ--ምን ብላ ትንገረዉ!፣

…………………እነዴት ትተርከዉ!፣

ቢሆንም ታሪክ ነዉ--ይወቀዉ ይረዳዉ፣

ፊርድ የሚሰጥበት--የነገ ሥራዉ ነዉ፣

…………………ብላ እያየችዉ፣

*"ባክህ ማሙሽዬ--ነገሩ እንዲህ ነዉ፣*

*ቆየ 'ኮ ከረመ--ቤታችን ወህኒ ነዉ፣*

*አንተን የወለድኩህ--እትብትህም ያለዉ፣*

*ባታዉቀዉም ቅሉ--እስር ቤት እኮ ነዉ!፣*

*አባትህም ባባ--እዛችዉ ቦታ ነዉ፣*

*ርቆ አልሄደም--እዛዉ እቤቱ ነዉ፣*

*ከሞቀ ኑሮዉ--አብርሮ ያመጣዉ፣*

*የሃገሩ ነገር--የወገን ፍቅር ነዉ፣*

*……………እናም እዚሁ ነዉ፣*

*እዚሁ ሀገሩ--እዚሁ እስር ቤት ነዉ፣*

*ታገስ ማሙሽዬ--ታሪኩ ብዙ ነዉ፣*

*በአምላክ ቸርነት--በነፃ ተፈጥረዉ፣*

*እንዳንተዉ ማሙሽን--ጩቅላቸዉን ትተዉ፣*

*ታስረዉ የሚኖሩ--ብዙ አባቶች ናቸዉ፤*

*ኦልባና ና አንዱዓለም--ፍትህ የራቃቸዉ፣*

*በቀለ ና ዉብሸት--እዉነት የጠማቸዉ፣*

*መቁጠር የሚታክት--ብዙ ዜጎች ናቸዉ፤*

*ይገባሃል ማሙሽ--ሁሉም እስር ቤት ነዉ!፤*

*አይዞህ ማሙሽዬ--አባትህ ጎበዝ ነዉ፣*

*ለኛም ለእነሱም--ለሁላችን ሲል ነዉ፤*

*ከኔ በፊት ሀገር--ወገኔ ብሎ ነዉ፣*

*እኔንም አንተንም--ታስሮ ሊያስፈታ ነዉ፤*

*ሀገርን ከ'ስር ቤት--እስር ቤትን ካገር…*

*……………………ታስሮ ሊለይ ነዉ::*

*ደግሞም ማሙሽዬ--ሌላም ሚስጥር አለዉ፣*

*ምናልባት አባትህ--ቢመረጥ እኮ ነዉ!፣*

*ከሌላዉ ለይቶ --ምሳሌ ሊያረገዉ፣*

*እሱን ሻማ አርጎት--ለሌላ ሊያበራዉ፣*

*በሱ ወህኒ መዉረድ--ሌላዉን ሊያስፈታዉ፣*

*ለዛም 'ኮ ይሆናል--ጨለማ የጣለዉ!፣*

*እንዴ ማሙሽዬ……………………!*

*የፈጣሪ ሥራ--ረቂቅ እኮ ነዉ!፣*

*እቺን የኛ ዓለም--ከጥፋት ያዳነዉ፣*

*የኛን ክፉ ሥራ--በደሙ ያጠበዉ፣*

*ያ የዓለም ጌታ--ሁሉን ያደረገዉ፣*

*እከብቶች ማደሪያ--በረት ተወልዶ ነዉ!::*

*የጥቁርን ዉርደት--መንግሎ የጣለዉ፣*

*ማንዴላ ሃገሩን--ባ'ለም ከፍ ያረገዉ፣*

*ሃያ ሰባት ዓመት--ታሥሮ ተገርፎ ነዉ!::"*

ብላ ስታወራዉ--ይሰቀጥጣታል፣

ይሄ ጨቅላ ህጻን--እንዴት ይገባዋል!፣

ሃገርን ከእሥር ቤት……………….

እሥር ቤትን ካገር--እንዴት የለየዋል?፣

ቢሆንም ግን ቅሉ--ማሙሽ ያስተዉላል፣

አባቱን ሊያይ ሲሄድ--ፖሊስ ይቆጣዋል፣

ከእቅፉ እንዳይቆይ--በብረት ተከቧል፣

ባባ ወጥቶ አይመጣ--በግረ ሙቅ ታሥሯል፣

እንዴት አያስጨንቅ………………!

ሁሉም ታሥሮ እያየ--ምኑን ይለየዋል!፣

ያባት ፍቅር ሳያይ--ሃገር እንዴት ያዉቃል!?

በምን መመዘኛ…………………….

ሃገር ተረካቢ--ተተኪ ይባላል?፣

እሥር ቤት ነዉ ሃገር--ምኑን ይረከባል!፣

እንኳን ለዚህ ጨቅላ--እኛም ቸግሮናል፣

እንኳን ለመናገር--መስማት ወንጀል ሆኗል፣

በገዛ ጣታችን--መጻፍ ያስጠይቃል፣

ዓይናችንም ላየዉ--አንቀጽ የጠቀሳል፣

በነፃ ተፈጥረን--ሆኖ አለመታደል፣

ዳግመኛ ነጻነት--ከሰዉ ይለመናል!፤

እንቆቅልሽ ነገር--እርግጥ ነዉ ይጨንቃል፣

ለዚህ ህፃን ጨቅላ--ለምን ይተረካል?!

ማሙሽ ግን ብልህ ነዉ--ተችሮት ማስተዋል፣

ሁሉንም ታዝቧል--ጠልቆ ተረድቶታል፣

መዝለል መቦረቁን--የልጅ ወጉን ትቷል፣

ይወጣል ይገባል--እናቱን ያያታል፣

እንደሰዉነቱ--እዉነት ይፈልጋል፣

ችላ ባትመልስም--ማሙሽ ይጠይቃል፣

*‘’ማማ ምን ይሻላል?*

*እኔም ባባን ሳክል--ፖሊስ ይወስደኛል?፣*

*ጨለማ ክፍል ዉስጥ--ይቆልፉብኛል?፣*

*ሰዉ እነዳላናግር--ይከለክሉኛል?፣*

*ቆይ ደሞ ማማዬ’’--ይላል ይቀጥላል፣*

*‘’ለወገኑ ሲል ነዉ--ያሰሩት ብለሻል፣*

*ይሄ ሁሉ ሥቃይ--ላገር ነዉ ብለሻል፣*

*እሱ እንዲህ ሲሆን--ወገኑ ግን የታል!?*

*ስሚኝ ባክሽ እናት……………………..!*

*እንደዚህ ናት ሃገር--እኔም የማድግባት?፣’’*

*ግን ለምን ወለድሽኝ--ምን ይሰራልኛል፣*

*ይላል ይገረማል--እናቱን ያያታል፣*

*መልስ ያጣ ጥያቄ--ምን መልስ ይኖራታል!፣*

እናት ታለቅሳለች--እሱም ይጠይቃል፣

**ህፃኑ ይጣራል--የአባት፡ የወገን፡ ያገር ያለህ ይላል፣**

ላባቱ ያልሆነ--ሀገር ያስፈራዋል፣

ያቅበጠብጠዋል--ይጣራል ይጮሃል!፣

የተኛችሁ ንቁ--የነቃችሁ በረቱ አንድ ሁኑ ይለናል፣

ማሙሽ እዉነቱን ነዉ--በጣም ያስጨንቃል፣

መዉለድ እስኪያስፈራ--መጪዉ ያሳስበል፣

ሀገር ለማቆየት--ተተኪ ለማብቀል፣

ከዚም ጫፍ ከዚያም ጫፍ--አርቆ ማስተወል፣

ከራስ በዘለለ--ማሰብ ያስፈልጋል፣

ደጋግሞ ደጋግሞ--መጨነቅ ይገባል፣

## የህፃኑ ጥሪ-------ምላሽ ይፈልጋል::

***እስክንድር ነጋን እና ሌሎች በግፍ የታሠሩ የህሊና እሥረኞችን ለማሰብ የተጻፈ!***

***አንዱዓለም በቀለ(Switzerland)2013.***